የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN
POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

ታህሳስ 5/2005

# የኢትዮጵያውያን መከራና ሰቆቃ በአፍሪካ እየተባባሰ ሄደ

በቅርቡ ወደ አፍሪካ ተጉዞ ያለው የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ልዑክ እንደገለጠ ው የኢትዮጵያ ስድተኞች ከኬንያ- ዩጋንዳ እስከ ደቡብ አፍሪካ ድረስ ከግድያ እስከ ስየልና ሰቆቃ እየ ደረሰበቸው መሆኑን አጋልጧል:: በርካቶች ለሞት በመዳረጋቸው ሰበብ አስባብ እየተሰጡ በየሞቱበት ሀገር ሲቀበሩ ሌሎች ደግሞ አስከሬናቸው ወደ ሀገር ቤት መላኩ ሊታወቅ ተችሏል:: የኢፖእአኮ ተጠ ሪ ባደረገው ጉብኝት አያሌ ስደተኞች በየማጎሪያዎቸ መከራ እየተቀበሉ መሆኑን ከማረጋገጡ ሌላ የባዕ ድ የሰብዓዊ መብት ጉዳይ ተቆርቋሪዎች ነን ያሉትም በኢትዮጵያውያን ላይ ስለሚደርሰው ጥቃት ደን ታ እንደሌላቸውም አረጋግጧል:: ልኡኩ በኬንያና ዩጋንዳ ከዚያም በደቡብ አፍሪካ የስደተኞችን ሁ ኔታ መርምሯል:: በአፍሪካ የኢፖእአኮ ስራ እየተካሄደ ሲሆን የሚቀናጅበትንና የሚጠናከርበትን ሁኔ ታ ለማረጋገጥም ተገቢውንና የተወሰነውን እርምጃ ወስዷል::

በኬንያና ዩጋንዳ ኢትዮጵያዊ ስደተኞች ብዙ እንግልት የሚደርሳባቸው ሲሆን ከወያኔ በተደረገ ስምምነ ት የተነሳም በርካታዎች ወይ ወደ እስር ተወርውረዋል አሊያም በግድ ለወያኔ ተሰጥተዋል:: የአፍሪካ እስር ቤቶች በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ስደተኞች ማጎሪያ እየሆኑ ናቸው:: ይህን በተመለከት የኢፖእአ ኮው ልኡክ በደቡብ አፍሪካ በተለይም በጆሃንስበርግ አካባቢ ሰንሲቲና ደመደት በተባሉት ቦታዎች በር ካታ እስረኞች እንዳሉ ሊያውቅ ችሏል:: የተወሰኑትንም እስር ቤት ሄዶ በማነጋገሩ አምኔስቲና የተባበ ሩት መንግሥታት የስደተኛ ኮሚሽን እየደረሰ ሰላለው ሰቆቃ ምንም ትችት ወይም ዘገባ እንዳለደረገ ሊ ረዳ ችሏል:: አቶ ታሪኩ አበበ (ካናዳዊ)፤ አቶ ኤልያስ ሱሌማን ሲራጅ ስደተኛ፤ አቶ ሰይፉ ጀምበሬ ሲ ራን (ሰደተኛና) ሌሎችም በህገወጥ መንገድ ለእስር ተዳርገው እንደሚማቅቁ ሊገነዘብም ችሏል:: የደቡ ብ አፍሪካ የፖለቲካ ቀውስ እየተባባሰ በመሄዱ የኤኮኖሚው ሁኔታ ያጠቃው ዜጋ ፀረ የውጭ ሀገር ዜጎችን ድብደባና ግድያ ላይ በመሰማራቱ አያሌ ኢትዮጵያውያን መገደላቸውና መጠቃታቸው የሚታወስ ነው::

ኢፖእአኮ በአፍሪካ እየተሰቃዩ ያሉትን ኢትዮጵያውያን በተቻለው ሁሉ ለመርዳት በሰፊው ሊንቀሳቀ ስም መነሳቱን ልዑኩ ገልጠዋል::


SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM
WEB SITE: WWW.SOCEPP.DE